# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 223 ነሐሴ 17 2004 ገጽ 1


በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት፣ በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ ትኩረት መሆን ያለበት መለስ ዜናዊ ጥሎት የሄደው አፋኝና ዘረኛ ሥርዓት መለስ ዜናዊን ተከትሎ ወደ መቃብር እንዲሄድ ትግሉን ማጠናከር ነው። አሁን ትግላችንን የምናፋፍምበት እንጂ "በነፍስ ይማር" ከንፈር የምንመጥበት ጊዜ አይደለም።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዱሞክራሲ ንቅናቄ የሙሆስ ዜናዊን ከዚህ አሁም በሞት ሙሆየት አስመሌከቶ መግሁጫ አወጣ

ንቅናቄው "የታላቅ አምባገነን ተራ ሞት" በሚል ርዕስ ባወጣው በዚህ መግለጫው ሃያ አንድ ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲያጭበረብርና ሲያምታታ የኖረው መለስ ዜናዊ ሞትን ማጭበርበርና ማምታት አቅቶት መሸነፉ በቃል አባይ፣ ቃል አቀባዮቹ ግልጽ መሆኑን ጠቅሶ "መለስ ይሙት እንጅ እሱ የዘረጋው የአፈና መዋቅርና የደነገጋቸው አፋኝ ህጎች ከመለስ ጋር አብረው እንዳልተቀበሩ አትቷል።

"በዘር ተሰባስበው ሃገርን የሚግጡና የሚረግጡ የጥቂት ግለሰቦች ቡድን ዛሬም በስልጣን ላይ ነው" ያለው የግንቦት 7 መግለጫ የዚህ ቡድን መሪ የሆነው መለስ ዜናዊ የዘራው የዘር መርዝ መዘዙ እንደተዳፈነ ያለ መሆኑንና ኅብረተሰባችን ውስጥ ያስፋፋው የሙስና ባህል እንደቆላ ቁስል ሃገር እየበላ መሆኑን፤ ሃገሪቱና ዜጎቿ የገቡበት የውርደት ጉዞ እንደቀጠለ መሆኑን እንዱሁም ድህነት፣ ስደት፣ የሙብት ረገጣ፣ አድሎ ከመለስ ዜናዊ ጋር አለመቀበራቸውን ገልጿል።

መግለጫው በመቀጠልም የኢትዮጵያ ሕዝብ መለስ ዜናዊ በጫንቃው ላይ የከመረበትን እኩይና ከፉ የኑሮ ሸክም እንደተሸከመ ያለ መሆኑን በመጥቀስ በዚህም የተነሳ የመለስ ዜናዊን ሞት ከቁብ ቆጥሮ ይህን የግፍ ቀንበር ከላዩ ላይ ለማውረድ ከጀመረው የነጻነት ትግል የሚዘናጋበት አንዳችም ምክንያት እንደሌለ ግልጽ አድርጓል።

የመግለጫውን ሙሉ ቃል በ4 ያንብቡ።

## ተቃዋሚ ድርጅቶች ያለፈዉ የግፍ ስርአት ተመልሶ የማይመጣ መሆኑን በትግላችን የምናሳይበት ወቅት ላይ እንገኛለን ሲሉ የግንቦት 7 የፍትህ፤ የነጻነትና የዱሞክራሲ ንቅናቄ ሊ/መንበር ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ና ዋና ጸሃፊው አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በየግል በሰጡት ቃለመጠይቅ ገለጡ

የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ሊቀመንበር የሆኑት ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ባለፈዉ ማክሰኞ ነሐሴ 15 ቀን 2004 ዓ.ም የመለስ ዜናዊን ከዚህ አለም በሞት መለየት አስመልክተዉ ከኢትዮጵያ ሳታሊይት ቴለቪዥን /ኢሳት/ ጋር ባደረጉት ቃለመጠይቅ "አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ የታየዉ የግፍ ስርአትና የኢትዮጵያ ህዝብ ያሳለፋቸዉ የግፍና የመከራ አመታት ተመልሰዉ የማይመጡ መሆናቸዉን ተቃዋሚ ድርጅቶች በትግላችን የምናሳይበት ወቅት ላይ እንገኛለን" ማለታቸው ተዘግቧል።

ከመለስ ዜናዊ ህልፈት በኋላ የተቃዋሚ ድርጅቶች የትግል አቅጣጫና ስልት ምን መምሰል እንዳለበት በጠቆሙበት በዚህ ንግግራቸዉ ዶ/ር ብርሀኑ ተቃዋሚዎች እስከዛሬ ወደ ኋላ ከጎተተን የ"እኔ ብቻ" ማንነት ተላቅቀን በጋራ በመታገል ትግሉን ከዳር የምናደርስበት ወሳኝ ግዜ አሁን ነዉ ብለዋል።

የመለስ ዜናዊ ከዚህ አለም በሞት መለየት በአገራችን ፖለቲካ ላይ ሊኖረው የሚችለው አንድምታ ካለ እንዲገልጹ የተጠየቁት ዶ/ር ብርሀኑ ሲመልሱ የመለስ መሞት ለአገራችን የፖለቲካ መድረክ ይዟቸዉ የሚመጣ መልካምና መጥፎ አጋጣሚዎች አንዳሉ ተናግረዉ ምንም አይነት መጥፎ ነገር እንዳይኖር ህዝባችንና ተቃዋሚ ፓርቲዎች አንድ ላይ በመሆን የስጋቱን ምንጭ ማስወገድ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

ለዚህም ደግሞ በኢትዮጵያ ስም የሚታገሉ የተለያዩ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዳሉ ገልጸዉ የእነዚህ ድርጅቶች የትግል ጥረትና እርስ በርስ እየተነጋገሩ በጋራ የሚያደርጓቸዉ እንቅስቃሴዎች የኢትዮጵያን የወደፊት እጣ ፋንታ ይወስናል ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል።

የመለስ ዜናዊን መሞት ተከትሎ ኢትዮጵያ ዉስጥ ሊፈጠር ስለሚችለዉ የስልጣን ክፍተትና ክፍተቱን ተከትሎ አገራችን አስፈላጊ ወዳልሆኑ አቅጣጫዎች እንዳትጓዝ ንቅናቄያቸዉ ምን አማራጮች አሉት ተብለዉ ለተጠየቁት ጥያቄ ዶ/ር ብርሀኑ ሲመልሱ ግንቦት ሰባት ሲመሰረት ጀምሮ የወያኔ ስርአት የሚወገድበትንና ስርዓቱ ከተወገደ በኋላ ሊኖር የሚገባዉን የሽግግር ግዜ አስመልክቶ ልንከተላቸዉ የሚገባንን አማራጮች ግልጽ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ መድረኮች ላይም ከህዝብ ጋር ተወያይቶባቸዋል ብለዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ግዜ

## ኢትዮጵያ ጳጳሰዋን እና መሪዋን በአንድ ሳምንት ልትቀብር ነዉ - የመለስ ዜናዊን ህልፈት ዜና አስመልክቶ ኢትዮጵያ ዉስጥ ዉጥረት ነግሷል

ላለፉት ሃያ አመታት አገራችንን በዘር፤ በሐይማኖትና በጎሳ ከፋፍሎ ኢትዮጵያን በጠመንጃ ኃይል የገዛዉ የመለስ ዜናዊና በመንፈሳዊዉ ዘርፍ አጋሩ ሆነዉ ለኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ቤ/ክርሲቲያን ሲኖዶስ ለሁለት መከፈል ምክንያት የሆኑት የብጹዕ አባ ጳዉልስ የቀብር ስነስርአት በአንድ ሳምንት ዉስጥ ሊፈጸም እንደሚችል ከአዲስ አበባ የደረሰን ዜና አስረዳ። ፓትሪያሪክ አባ ጳዉሎስ ከዚህ አለም በሞት የተለዩት ባለፈዉ ሳምንት ሐሙስ ማለዳዉ ላይ ሲሆን መለስ ዜናዊ ግን ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ቴላቪዥን ሞተ ተብሎ የተነገረዉ እሁድ ለሊት ነዉ ቢባልም መለስ ዜናዊ ከሳምንታት በፊት ብራሰልስ ሆስፒታል ዉስጥ መሞቱን የሚያረጋግጡ ብዙ መረጃዎች መኖራቸዉ ተረጋግጧል።

የወጣትነት ዕድሜዉን በትግል ያሳለፈዉ መለስ ዜናዊና አብዛኛዉን የዕድሜ ዘመናቸዉን ፈጣሪያቸዉን በማገልገልና የመንፈሳዊዉንና የገሀደን አለም ትምህርት በማማር ያሳለፉት አባ ጳዉሎስ በችግር ትማቅቅ ለነበረችዉ ኢትዮጵያ መፍትሄ ይሆናሉ ተብሎ ታምኖ ነበር። ሆኖም እነዚህ በተለያየ ግዜ በአንድ አካባቢ ተወሌደዉ ያደጉ ሰዎች ከአገራቸዉ የወደፊት ራዕይ ይልቅ ለወንዜ ልጅነትና ለዚህ አለም ጥቅም ስሰተገዙ አገራችንን አይታዉ የማታዉቀዉ የፖለተካና የማህበራዊ ቀዉስ ዉስጥ ከትተዋት አልፈዋል። የመለስ ዜናዊና የአባ ጳዉሎስ መደጋገፍ ለገዳማት መደፈርና መዘረፍ፤ ለብዙዎች መታሰር፤ ለሰቆቃና ግድያ እንዲሁም አገራችን ዉሰጥ ዛሬ ለሚታየዉ የሞራልና ግብረገብነት ዉድቀት አስተዋጽኦ አድርጓል የሚሉ እጅግ በጣም ብዙ ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ። የእነዚህ ትግራይ አድዋ ዉስጥ ተወልደዉ በተመሳሳይ ወቅት ስልጣን ላይ የወጡ ሰዎች በአንድ ወቅት ሞተዉ በአንድ ሳምንት ዉስጥ ለቀብር መብቃታቸዉ የመለኮት ስራ ነዉ የሚሉ ብዙ የእምነት ሰዎች እንዳሉ ከአዲሰ አበባና ከየክልሉ የሚመጡ ዜናዎች ያመለክታለ። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ተደብቆ የከረመው የዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ዕልፈተ ሞት ይፋ ሆነ። አለም አቀፍ ሚዲያዎች የፖለቲካ ሙብት አፋኝ እንደነበረ ገና ከአሁኑ መዘገብ ጀምረዋል

አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ በዘረኝነትና በዝርፊያ ላይ የተመሰረተ የኤኮኖሚ ስርአት ገንብቶ ሀያ አንድ አመት ሙሉ ህዝብን ሲያሰቃይ የከረመዉን የመለስ ዜናዊን ከዚህ አለም በሞት መለየት የወያኔ አገዛዝ ይፋ አደረገ።

ቀደም ሲል የአልባኒያ ኮሚኒዝም አቀንቃኝ የነበረው መለስ ዜናዊ ዲሞክረሲ እገነባለሁ እያለ አገሪቱን ታይቶ ወደማይታወቅ አምባገነንነትና የረከሰ ዘረኝነት አዘቅት ዉስጥ ሲከታት ከኖረ ቦኋላ በሰኔ ወር ውስጥ በጠና ታሞ ቤልጂዬም ብራስልስ በሚገኘው የሴንት ሉክ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ስታከም ከቆየ ቦኋላ በሃምሌ ወር መጨረሻ አካባቢ ከዚህ አለም በሞት እንደተለየ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘ መረጃ ይፋ አድርጎ እንደነበር የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ዘግቦት እንደነበር ይታወቃል። ሆኖም ግን ቱባ ቱባ የወያኔ ባለሥልጣናት የሰውየውን በጠና መታመም ሲክዱ ከሰነበቱ ቦኋላ የመሞቱ ዜና በህብረተሰቡ ዘንድ መሰራጨቱን እንደሰሙ መታመሙን አምነው በመልካም ጤንነት ላይ ይገኛል ሲሉ ማስተባቢያ ሲሰጡ እንደሰነበቱ ይታወሳል።

በረከት ስሞን ባለፈው ሳምንት ለአገር ውስጥና ለውጪ ጋዘጠኞች በሰጠው መግለጫ ይባስ ብሎ መለስ ዜናዊ ከህመሙ ያገገመ በመሆኑ ከአዲሱ አመት በፊት ሥራው ላይ ይመለሳል ብሎ እንደነበር ይታወቃል።

ላለፉት ሶስት ሳምንታት የመለስ ዜናዊን ከዚህ አለም በሞት መለየት በከፍተኛ ሚስጥር ለመጠበቅ ከንቱ ሙከራ ሲያደርግ የቆየው የበረከት ቡድን በዛሬው ዕለት ማግስት ላይ በወያኔ ቁጥጥር ሥር በሚካሄደው ሬዲዮና ቴለቪዥን አማካኝነት ለህዝብ ይፋ ከካደረገ ቦኋላ በርካታ የአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ዜናውን ተቀባብለው በማሰራጨት ላይ ይገኛሉ።

የሚዲያዎች ሲጠብቅ የነበረው የወያኔ ቡድን መሞት በትልቅ እንደሚመለስ መናገሩ ዜናዊ ቀኝ እጅና

መታመምና ብሎም የመሞቱ ዜና ከተሰማ የሰነበተ ቢሆንም ዉሸታሞቹ የወያኔ መሪዎች ግን "መለስ ዜናዊ በአዲሱ አመት ስራዉን ይጀምራል" ብለዉ በተናገሩበት አፍ ደብቀዉ ማቆየት የማይችሉትን የመለስ ዜናዊን ህልፈተ ዜና ሳይወዱ በግድ ለህዝብ ይፋ አድርገዋል።

በአለም ታዋቂ የሆኑት የዜና አውታሮች ስለ መለስ ዜናዊ ህልፈት ባደረጉት ልዩ ዘገባ አንዳንድ የአፍሪካ አምባገነኖች የኢኮኖሚ ልማት ያስመዘገበና ለአፍሪካ ተቆርቋሪ የሆነ መሪ በማለት ሲያወድሱት በአገራቸው (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የመለስ ዜናዊ ለቅሶ ድራማ እና ዘላቂው መፍትሄ

የዘረኛውና የአምባገነኑ መለስ ዜናዊ መሞት በይፋ ታወጀ። ቤተሰቦቹና ባልደረቦቹ፤ አጨብጫቢዎችና አስመሳዮች እና በርካታ የዋህ ዜጎች ሃዘናቸውን በመግለጽ ላይ ናቸው።

የመለስ ዜናዊ ሞት እወጃን ጨምሮ አብዛኛው ነገር የተለመደ ድራማ መሆኑ ቢታወቅም እንኳን፣ ደጉ የኢትዮጵያ ሕዝብ "ነብስ ይማር፤ እግዚአብሄር ያጥናችሁ" ማለቱ አልቀረም።

የለቅሶው ድራማ ሰሜን ኮሪያን ቢያስታውሰንም እዚያ ከነበረው በላይ የሚያሳምም ነገር አለው። ንጹሃን ዜጎችን በማሰቃየትና በመግደል የሚታወቁ፤ ትኩስ የሰው ደም በእጃቸው ላይ ያለ የወያኔ ሹማምንት በአለቃቸው ሞት ሲያነቡ ማየት የሚያስተዛዝብ ብቻ ሳይሆን የሚያሳዝን ነው። ይህ ተግባራቸው ብቻውን እነሱ "ሰው" ብለው የሚጠሩት ፍጡር የኢትዮጵያ ሕዝብን በሙሉ የማያጠቃልል መሆኑ ማረጋገጫ ነው። ለዚህም ነው ያለአንዳች ርህራሄ ህፃናትን ሲጨፈጭፉ የኖሩ ፋሽስቶች ለጌታቸው ሞት በአደባባይ ሲያነቡ የሚታዩት። እነዚህ ጨካኞች በየጎዳናውና በየጥሻው በግፍ ገድለው የጣሏቸው ኢትዮጵያዊያን፤ አሁንም በግፍ በየእስር ቤቱ ያጓሯቸው ንጹሃን የሚያዝኑና የሚያለቅሱ ቤተሰቦች ያሏቸው መሆኑ አይታሰባቸውም። የእነሱ ዘር አባል ያልሆነ፤ አሊያም ለእነሱ ያልገበረ ሁሉ "ሰው" አይደለምና ህመሙ አይታያቸውም፤ ለቅሶው አይሰማቸውም። ለእነሱ "ሰው" ማለት የእነሱ የሆነ ሰው ማለት ብቻ ነው። እነሱ "ሰው" ከሚሉት ውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ መረገጡ፣ መገረፉ፣ መገፋቱ፣ መፈናቀሉ፣ መጋዙ፣ መገደሉ ተገቢ ነገር ነው። ከእነሱ አንዱ አደጋ ከደረሰበት ግን የሚያሳዝንና የሚያስለቅስ ነገር ነው። ይህ ነው በመለስ ዜናዊ የለቅሶ ድራማ ውስጥ እያየነው ያለ ሃቅ።

አዎ መለስ ዜናዊ ሞቷል። እሱ የዘረጋው ዘረኝነት እና ዘረኛ ፓሊሲው የቆመባቸው የአፈና መዋቅር አብረውት አልሞቱም። በዘር ተሰባስበው በኢትዮጵያዊያን ላይ የሚያላግጡ፤ ሃገርን የሚግጡና የሚረግጡ ግለሰቦች ቡድን ዛሬም በስልጣን ላይ ነው። መለስ የዘራው የዘረኝነት መርዝ መዘዙ ብዙ ነው። ይህ መርዝ ነቅለን ካልጣን በስተቀር ከመለስ ሞት በኋላም ቢሆን በማኅበረሰባችን እና በሃገራችን ላይ ጉዳት ማድረሱ ይቀጥላል። ዘረኝነት በሁሉም ቦታ - በለቅሶም ጭምር - ኢትዮጵያዊያንን ማዋረዱ የማይቀር ነው። የመለስ አገዛዝ ከመለስ ዜናዊ ጋር እስካልቀበርነው ድረስ የሚደርስብን ጥቃት ይጨምር እንደሆነ እንጂ አይቀንስም። ስለሆነም ከዘረኝነት ጋር የገጠምነው ትግል አጠናክረን መቀጠል ግዴታችን ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ መለስ ዜናዊ ከጫነበት የዘረኝነት እና የባርነት ስቃይ ሳይገላገል የመለስ ዜናዊን ሞት ከቁብ ቆጥሮ ከጀመረው የነፃነትና የእኩልነት ትግል የሚዘናጋበት ምክንያት የለውም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በመለስ ዜናዊ ሞት ዙሪያ የሃገር ውስጥና የውጭ ሃገራት ጥቅም ተካፋዮቹ የሚሰሩትን ትዕይንት በማየትና በመስማት የሚያጠፋው ግዜ ሊኖር አይገባም።

በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት፣ በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ ትኩረት መሆን ያለበት መለስ ዜናዊ ጥሎት የሄደው አፋኝና ዘረኛ ሥርዓት መለስ ዜናዊን ተከትሎ ወደ መቃብር እንዲሄድ ትግሉን ማጠናከር ነው። አሁን ትግላችንን የምናፋፍምበት እንጂ "በነፍስ ይማር" ከንፈር የምንመጥበት ጊዜ አይደለም።

ስለሆነም ግንቦት 7:

- መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመለስ ዜናዊ ዜና እረፍት እና ተያይዞ በሚመጣው ድራማ ሳይዘናጋ መሠረታዊ ለውጥ በኢትዮጵያ እንዲመጣ ትግሉን እንዲያጠናክር፤
- የመከላከያ ሠራዊት አባላት የሕዝብ ወገንተኝነታቸውን ተገንዝበው አውራውን በማጣት እየተንገዳገደ ያለውን ወያኔ በማስገደድ ወይም በማስወገድ ሥራ ላይ የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲያደርግ፤
- ህሊና ያላቸው የወያኔ ባለሚሎች ራሳቸውን ከወያኔ አግልለው የሕዝብን ትግል እንዲቀላቀሉ፤
- ፍትህ፣ ነፃነት፣ እኩልነትና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ እንዲሰፍኑ የሚፈልጉ ወገኖች ሁሉ ኃይላቸው እንዲያስተባብሩ ወገናዊ ጥሪ ያቀርባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## ህዝባችንን በመርዛማ ጋዝ ለፈጀው የፋሽስት ጣሊያን ጄነራል ግራዚያኒ በጣሊያን ከተማ የክብር መታሰቢያ መናፈሻና ሙዚዬም መገንባቱን በመቃወም ግንቦት 7 ለጣሊያን መንግሥት የተቃውሞ ደብዳቤ አስገባ

ቁጥሩ በውል የማይታወቅ ህዝባችንን በአለም በተከለከለ መርዛማ ጋዝ ለፈጀው የፋሺስት ኢጣሊያ ጀኔራል ግራዚያኒ ከሮማ ከተማ በስተደቡብ በምትገኘው የአፊላ መንደር ውስጥ የክብር መታሰቢያ መናፈሻና ሙዚዬም መገንባቱ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ፋሽስቶች በህዝባችን ላይ ያደረሱትን ወንጀል እንደማወደስ የሚቆጠር ስለሆነ ለመታሰቢያነት የተሰራው ይህ መናፈሻና ሙዚዬም በአስቸኳይ እንዲፈርስ ወይም ሌላ ሥም እንዲሰጠው በመጠየቅ ግንቦት 7 የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለጣሊያን መንግሥት የተቃውሞ ደብዳቤ አስገባ።

በወቅቱ የሊግ ኦፍ ኔሽን አባል የሆነቺውን ነጻ አገራችንን ሉአላዊነት በመጣስ በአገራችን ላይ የ እብሪት ወረራ የፈጸመው የፋሽስቱ ጣሊያን ጦር አዛዥ የነበረው ግራዚያኒ ፍጹም ሪህራሄ በጎደለው ጭካኔ በአለም አቀፍ ህግ የተከለከለውን መርዘኛ ጋዝ እራሱን ለመከላከል የሚያስችል ምንም አይነት ዘመናዊ መሳሪያ ባልታጠቀ ህዝባችን ላይ መጠቀሙ መቼውንም ቢሆን ሊሻር የማይችል ጠባሳ ጥሎ አልፎአል ያለው የግንቦት 7 የተቃውሞ ደብዳቤ ፤ በሰለጠነው 21ኛው ክፍለ ዘመን የሚኖረው የአሁኑ የጣሊያን መንግሥት በታሪክ አሳፋሪ ተግባር ለፈጸመው ለፋሽስቱ ሞሶሎኒ ጦር አዛዥ ለግራዚያን እንዲህ አይነት የክብር መታሰቢያ በዋና ከተማው ማቆም ለህዝባችንና ለአገራችን ያለውን ንቀት እንደማሳየት ይቆጠራል ብሎአል።

የተቃውሞ ደብዳቤውም በመቀጠልም፤ የጣሊያንንና የሌሎችን አውሮጳዊያን ቅኝ ገዥነትን በጽናት ስትከላከል የኖረችውና በትግሏ ነጻነቷን አስከብራ ለመኖር የቻለቺው አገራችን ምንም እንኳ ከውስጧ በበቀሉ የአገር ጠላቶች አገዛዝ ሥር በመውደቋ የተነሳ ይህንን የጣሊያንን መንግሥት ድርጊት በአፍሴል የሚቃውምና የክብር መታሰቢያው በአስቸኳይ እንዲፈርስ የሚጠይቅላት መንግሥት ለጊዘው ባይኖራትም ህዝባችን ለክብሩና ለነጻነቱ የሚቆረቆር የራሱ መንግሥት ሲመሰርት በሁለቱ አገሮች መካከል ጥላቻን የሚቀሰቅስ ተግባር እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል ሲል አስጠንቅቆአል።

አድማጮቻችን ንቅናቄያችን ለጣሊያን መንግሥት ያስገባውን የተቃውሞ ደብዳቤ ሙሉ ቃል ትርጉም በሃሙስ ፕሮግራማችን ይዘን የምናቀርብ መሆናችንን ከወዲሁ እንገልጻለን።

## የኢድ አልፈጥርን በዓል ምክንያት በማድረግ ለስግደት በአዲስ አበባ ስታዲዮም የተገኙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ድምጻቸው እንዲሰማ በመጠየቅ ከፍተኛ ታቃውሞ አሰሙ። ፖሊስ በሴቶች፤ በህጻናትና; በሽማግሌዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰ

ዘጋቢያችን ከስፍራው እንደገለጸው የሙስሊሙ ማህበረሰብ አባላት ወደ አዲስ አበባ ስታዲዮም መትመም የጀመሩት ከጠዋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ ሲሆን በስፍራው እንደደረሱ ጥብቅ ፍተሻ እየተደረገባቸው እንዲገቡ ተደርገዋል። ይሁንና ፍተሻውና በአካባቢው ተበትነው ውጥረት ለመፍጠርና ለማስፈራራት የሞከሩት የፖሊስና የደህንነት አባላት እንቅስቃሴ ተቃውሚቸውን እንዳያሰሙ ሊያግዷቸው አልቻሉም።

በመሆኑም በበዓሉ ላይ የተለመደውን አደንቋሪ ወያኔያዊ ፕሮፓጋንዳ ለማሰማት በቦታው የተገኘው ኩማ ደመቅሳ ንግግሩን በወጉ ሳያቀርብ በተቃውሞው ድምጽ ተውጦ ቀርቷል።

ነጭ መሃረብ በማውለብለብና እጅ ለእጅ በመያያዝ ፍጹም ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ የተቃውሞ ድምጻቸውን ያሰሙት እነዚሁ ሙስሊም ዜጎች "ድምጻችን ይሰማ" " የታሰሩት የኮሚቴ አባላት ይፈቱ" "ምርጫችን በመስጊዳችን" የሚሉና ሌሎችንም በርካታ መፈክሮች አስተጋብተዋል።

የአዲስ አበባ ስታዲዮም ፕሮግራም ተጠናቅቆ ወደየቤታቸው ሲመለሱ ተመሳሳይ መፈክሮችን እያሰሙ መጓዛቸውን የገለጸው ዘጋቢያችን በተለይም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በራፍ ላይ ያለፉት ሙስሊሞች "ውሽታሞች" "ውሸት ሰለቸን" የሚሉ መፈክሮችን ማስተጋባታቸውን አብራርቷል።

ከነዚሁ በልዩ ልዩ አቅጣጫ ወደ መኖሪያቸው ተመላሽ ሙስሊሞች መካከል የተወሰኑት የሲቪል ልብስ በለበሱ ሰላዮች ተይዘው መታሰራቸው ታውቋል።

ዘጋቢያችን ለምን የወያኔውን ቡችላ ኩማ ደመቅሳን ንግግር ለማዳመጥ እንዳልፈለጉ የጠየቃቸው አንድ የበዓሉ እድምተኛ በመጀመሪያ ምንም ስልጣን ስሌለው የሚደሰኩርልን የተነገረውን የተለመደ ፕሮፓጋንዳ እንጂ ከኛ ጥያቄ ጋር በተያያዘ የመፍትሄ ሃሳብ እንደማይሆን ስለምናውቅ፣ በሁለተኛ ደረጃ እስከ ዛሬ ጥቂቶች ናችሁ እያሉን ነበር፣ እና እኛ ጥቂቶቹ ጋ ምን ያደርጋሉ ብዙሃኑ ጋ ሄደው ንግግር ያድርጉ በሚል ነው ብለዋል።

በተመሳሳይም በናዝሬት፣ በደሴ፣ በጅማና በሌሎችም የሀገሪቱ ከተሞች በዓሉን ለማክበር የተሰባሰቡት ሙስሊሞች እነዚያኑ የመላ ሙስሊሙን የሙብት ጥያቄዎችን በማንሳት ተቃውሚቸውን ማሰማታቸው ተዘግቧል።

## ተደብቆ የከረመው የዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ዕልፈተ ሞት ይፋ ... (ከገፅ 1 የዞረ)

ውስጥ ለህዝባቸው ሰፋ ያለ ነጻነት የሰጡ መንግሥታት ተወካዮች ግን የአገሩን ህዝብ ሙብት በማፈንና የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን በማሳደድ ይታወቃል ሲሉ አስተያየት መስጠታቸውን መዝግበዋል።

መለስ ዜናዊ ድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው ጭፍጨፋ፤ በፋይዳ ቢሱ የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ሰበብ ስላስገደላቸው ከመቶ ሺህ በላይ ወጣቶች በተከታታይ እየዘገቡ እንደሆነም የዝግጅት ክፍልዝችን ያደረጋቸው ዳሰሳዎች ያመለክታሉ።

በመለስ ዜናዊ ዘረኛ ፖሊሲ ላለፉት 21 አመት ዋጋ ሲከፍል የኖረው ህዝባችን መለስን የሚያስታውሰው በከፋፋይነቱና የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ ለባዕዳን በመስጠቱ ነው።

አንዳንድ የአገር ዉስጥና የምዕራቡ አለም የፖለቲካ ተንተኞች የመለስ ዜናዊ መወገድ ለኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ግንባት ሂደት መንገድ ይከፍታል የሚል እምነት ቢኖራቸዉም መለስ ዜናዊ የዘረጋዉ ዘረኛ ስርአትና አብረዉት ስርአቱን የገነቡት ዘረኞች ጓደኞቹ እስካሉ ድረስ ኢትዮጵያ ዉስጥ ስለ ዲሞክራሲ ማሰብ እንደማይቻል ብዙዎች በአጽንኦት ይናገራሉ። በዚህ አጋጣሚ ግንቦት ሰባት የፍትህ፤የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የኢትዮጵያ ህዝብ በምንም ነገር ሳይዘናጋና ካለፉት ሁለት የስልጣን ሽግግሮች ስህተቶች በመማር የጀመረዉን የነፃነት፤ የእኩልነትና የደሞክራሲ ትግል ከግቡ ለማድረስ በቆራጥነት እንዲታገል ጥሪ ማድረጉን ከንቅናቄዉ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

---

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

# ከጥሩ ወደ ታላቅ

## አንዳንድ ድርጅቶች ታላቅ ለውጥ ማምጣት ሲችሉ ሌሎቹ የሚያቅታቸው ለምንድነው?

በንቅናቄዓችን ትምህርትና ሥልጠና የተዘጋጀ ( ክፍል 3)

### ምዕራፍ V: የጃርቷ ነገረ-ሃሳብ /The Hedgehog Concept/

ስለጃርት እና ቀበሮ የተነገረውን ጥንታዊውን የግሪክን ተረትን ያስታውሳሉ?

ቀበሮ ብልህና ብልጥ ነው። በጣም ብዙ ነገር ያውቃል። ጃርት ግን የዋህ ቢጤ ናት። ጃርት ጠንቅቃ የምታውቀው አንድ አቢይ ጉዳይ ብቻ ነው - አደጋ በሚመጣበት ወቅት ራስዋን በሾህዎቸዋ መሸፈን። በቃ፤ የጃርቷ እውቀትም ችሎታም ይኸ ብቻ ነው።

ቀበሮ ጃርትን ለማጥቃት ውስብስብ እቅዶችን ያወጣል፤ ስትራቴጂዎችን ይነድፋል። እቅዱን የሚያሳካበት ምቹ ጊዜ እስኪያገኝ በጃርት መኖሪያ ዙርያ ያንዣብባል። ጃርት ግን ስለቀበሮ ውስብስብ እቅድ እውቀትም ግድም ሳይኖራት ውስብስብነት የሌለው የዕለት ተዕለት ሕይወትዋን ትመራለች።

ቀበሮ በውስብስቡ ጥናቱ እየተመራ ምቹ ባለው ጊዜ ዘሎ ጉብ ሲልባት ሲል ጃርት ሾሆችዋን ታቆማለች። "አይ አሁን ነቃሽብኝ! ቆይ አገኝሻለሁ፤ ጠብቂ!!!" ይላታል ቀበሮ። በሌላ ቀን አድብቶ ይሞክራል፤ አሁን ጃርት ትቀድመዋለች። እንዲህ እንደተባለ ክረምትና በጋ ይፈራረቃሉ፤ ዓመታት ይነጉዳሉ። ጃርት የምታውቀው አደጋ ሲኖር ሾህዎቸዋን ማቆም ብቻ ነው። ስለ ቀበሮ እቅድም ሆነ ስትራቴጂ የምታውቀው ነገር የላትም። አደጋ ሲቃጣባት ግን ፈጥና እርምጃ ትወስዳለች። ታድያ ሁሌም የምታሸንፈው ጃርት ነች።

ይህ ምሳሌ ምን ይነግረናል? ብዙ ድርጅቶች ብዙ ጉዳዮችን ይዘው ይዳክራሉ። አንዳንዶች ደግሞ አንድ ዋና ሥራ ይዘው በሱ ይሰለጥናሉ።

ታላቅ ድርጅትን ለመገንባት እንደ ጃርቷ መሆን ያስፈልጋል።

ከጥሩ ወደ ታላቅነት የተሸጋገሩ ድርጅቶች ከሌሎቹ በሁለት መሠረታዊ ነገሮች ይለያሉ

1. ስትራቴጂዎቻቸው በሶስት ዋና ዋና ነገሮች ላይ ያተኩራሉ - መሥራት በሚችሉት፤ መሥራት በሚወዱት እና ውጤቱ በሚያጓጓቸው ጉዳዮች።
2. ይህን ስትራቴጂ በቀላሉ መረዳት ወደሚቻል አንድ አጠቃላይ መርህ ያወርዱታል (እንደ ጃርቷ የመከላከል ስትራቴጂ)

የጃርቷን ምሳሌ ለመከተል ድርጅቶች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ

1. ምንድነው አሳምረን መሥራት የምንችለው? (ምንድነው አሳምረን መሥራት የማንችለው?)
2. ምንድነው የውጤታችን ምንጭ? ምንድነው ለታላቅ ውጤት የሚያበረታታን ነገር? ውጤት የምለው ነገር በአንድ ነገር ብቻ ይለካ ቢባል ያ ነገር ምንድነው?
3. ምንድነው በጣም የምንወደው ሥራ ምንድነው? ውጫዊ ማነቃቂያ የማይፈልግ ሥራ? ሥራው መሠራቱ ብቻውን ማነቃቂያችን የሆነው እርሱ ምንድነው?




የጃርቷ ምሳሌ የሚያስረዳን አሸናፊ የሚያደርገን ምርጥ ስትራቴጂ፣ ምርጥ ግብ ወይም ምርጥ ፕላን ስላለን ሳይሆን የምንሠራውን ሥራ ጠንቅቀን ስናውቅ፤ ሥራችንን ስናፈቅርና፤ በሥራችን ስንነቃቃ ነው። ሶስቱ ክቦች በሚገናኙበት ቦታ ላይ ያተኮረ ድርጅት ታላቅ ድርጅት የመሆኑ እድሉ እጅግ የሰፋ ነው።

በጥሩ ሁኔታ የሚሠሩት ነገር የድርጅትዎ ዋነኛ ሥራ ካልሆነ እርስዎና ድርጅትዎ አልተገናኙም ማለት ነው። በጥሩ ሁኔታ የሚሠሩት ነገር የድርጅትዎ ዋነኛ ሥራ ከሆነ ደግሞ የጃርቷን ምሳሌ ይከተሉ። ትኩረትዎን በሙሉ እዚያ ላይ ያድርጉ። ጃርቷን መሆን ማለት የድርጅቱን ውጤታማነት በሚወስነው ዋነኛ ሥራ ላይ ጊዜና ጉልበትን ማጥፋት ማለት ነው፤ ትኩረትን ማሰባሰብ ማለት ነው።

የድርጅቱ አመራር ዋነኛ ሥራ ድርጅቱን "ጃርት" ማድረግ ነው።

### ምዕራፍ VI: ሥነሥርዓትን ባህል ማድረግ /A Culture of Discipline/

ከጥሩ ወደ ታላቅነት የተሸጋገሩ ድርጅቶች በሙሉ ጥብቅ ድርጅታዊ ዲሲፕሊን ድርጅታዊ ባህል የሆነባቸው ናቸው።

በተለይም የሚከተሉት እጅግ አስፈላጊ ናቸው

1. በነፃነት፣ ኃላፊነት እና በመዋቅር ጉዳዮች ላይ ጠንካራ ዲሲፕሊንና ባህል መገንባት፤
2. ይህንን ባህል ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ርቀው ለመጓዝ ዝግጁ በሆነ ሰዎች የግል ዲሲፕሊን መገንባት፤
3. ድርጅታዊ ዲሲፕሊንና ባህልን ከአምባገነናዊ ዲሲፕሊን አለማደባለቅ፣ እና
4. የጃርቷን ምሳሌ ሁሌ ተግባራዊ ማድረግ። ትኩረት ሊሰጠው በሚገባ ጉዳይ ላይ የሃይማኖት ያህል ጥብቅነት መፍጠር። የዚህኑ ያህል "ይህ እኛ ዘንድ አይሠራም፤ አይፈለግም" የሚባሉ ነገሮችን ዝርዝር ማዘጋጀት

ከጥሩ ወደ ታላቅነት በሚሸጋገሩ ድርጅቶች ውስጥ የሚታወቁ ገደቦች ያሉባቸው ሥርዓቶች (systems) አሉ። በእነዚህ ሥርዓቶች ውስጥ ግን ነፃነትና ኃላፊነት አሉ። እነዚህ ድርጅቶች ራሳቸውን በራሳቸው መምራት የሚችሉ ሰዎች አሉዋቸው። በዚህም ምክንያት በታላላቅ ድርጅቶች ውስጥ ሥርዓቶችን (ሲስተሞችን) እንጂ ሰዎችን ማኔጅ ማድረግ አያስፈልግም። የዚህ ጥናት አንዱ ግኝት የዲሲፕሊን ባህል ለድርጅት ታላቅነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ማስገንዘብ ነው።

ወደ ታላቅነት ሽግግር የሚጀመረው ራሳቸውን በራሳቸው ሥርዓት ማስያዝ (ራሳቸውን ማስተዳደር) የሚችሉ ሰዎችን በመምረጥ እንጂ ሥርዓት የለሽ ሰዎችን ሥርዓት በማስያዝ አይደለም። በድርጅት ውስጥ ዲስፕሊን መኖሩ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ራሳቸውን ሥርዓት ማስያዝ የሚችሉ ሰዎች የሞሉበት ከሆነ ድርጅቱ መራር ተግዳሮቶችን መጋፈጥ ይችላል።

መሪዎች ለጠንካራ ዲሲፕሊን የጃርቷን አርዓያነት እንደ ድጋም (mantra) መቀበል ይኖርባቸዋል። "ከዋነኛ ሥራችን ጋር ተያያዥነት ለሌለው ጉዳይ የምናባክነው ጊዜ የለም" "ይሄ የኛ ሥራ አይደለም" "ይሄ ለኛ አይሆንም" የሚሉ እና የመሳሰሉ ዓረፍተ ነገሮች መለመድ አለባቸው።

ብዙዎች መጥፎ እና መካከለኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ ድርጅቶች ጊዜዓቸውና ኃይላቸውን የሚያጠፉት በማይጠቅማቸው ሥራ ላይ ነው።

### ምዕራፍ VII: ቴክኖሎጂ /Technology Accelerators/

ጥሩ ቴክኖሎጂ ወደ ስኬት የሚደረግን ጉዞ ሊያፋጥን ይችላል፤ የስኬት ምንጭ ግን አይደለም። ከጥሩ ወደ ታላቅነት የሚሸጋገሩ ድርጅቶች የማያውቁትን ቴክኖሎጂ አዲስ ስለሆነ ብቻ አይጠቀሙም። ቢያንስ የአዲሱ ቴክኖሎጂ ጥቅምና ጉዳት እስኪያውቁ ይጠብቃሉ።

በቴክኖሎጂ ምርጫ ወቅት "ይህ ቴክኖሎጂ ድርጅቴን ጃርቷን ለማድረግ ይጠቅመኛልን? (ዋናኛውን ሥራዬን ለማከናወን ይጠቅመኛልን?)" ብሎ መጠየቅ ይገባል። መልሱ አዎ ካልሆነ ቴክኖሎጂውን አለመጠቀም ይሻላል።

### ምዕራፍ VIII: መዘውር እና መሰናከል /The Flywheel and the Doom Loop/

በጣም ከፍተኛ ክብደት ያለው መዘውር ለማሽከርከር ሞክረው ያውቃሉ?

ከባድ መዘውር ከቆመበት ማንቀሳቀስ በጣም፣ እጅግ በጣም ከባድ ነው። ያም ሆኖ ግን ተጣጥረው ያንቀሳቅሱታል። ትንሽ ከተንቀሳቀሰልዎች እንዳዩቆም ፋታ ሳይሰጡ መግፋትዋን ይቀጥሉ። እንደምንም አንድ ዙር ያዞሩት .... ሁለተኛውን ይድገሙ ... ሶስተኛውን ይድገሙ ... አራተኛ ...አምስተኛ ...ስድስተኛ ... በእያንዳንዱ ተጨማሪ ዙር እየቀለልዎት ይመጣል ... ይቀጥሉ ... ሃያኛ ... አምሳኛ ... በሆነ ወቅት መዘውሩ ራሱ መሽከርከር ይጀምራል።

መዘውሩ ራሱ መሽከርከር ከጀመረ በኋላ ከባድ መሆኑ የሚጠቅምዎት እርሶን ነው። ከባድ መዘውር አንዴ መዞር ከጀመረ በቀላሉ አይቆምም። እየዞረ እያለ ትንሽ ተጨማሪ ግፊት ከጨመሩለት ግዙፉ መዘዉር በከፍተኛ ፍጥነት ይውለበለብልዎታል።

አሁን እንበልና አንድ ሰው ይመጣና "የትኛው ግፊት ነው ትልቁን ለውጥ ያመጣው?" ብሎ ቢጠይቅዎ ምን ብለው ይመልሳሉ? የመጀመሪያው? የሁለተኛው? አምስተኛው? ሠላሳኛው? ማንም ለይቶ መናገር አይችልም። ሁሉም ተባብረው ነው እሽከርክሪቱን እዚህ ደረጃ ላይ ያደረሱት። ያለን ድርጅትን "መቀስቀስ" ከባድ ነው። ሆኖም አንዴ መለወጥ፣ ማደግ ከጀመረ በየጊዜ እየተገነባ ወደ ታላቅነት መድረስ ይቻላል።

ከጥሩ ወደ ታላቅነት የሚሸጋገሩ ድርጅቶች ተከታታይ መሻሻል የማምጣትን ጥቅም የተረዱ ናቸው። የማቋርጥ ተከታታይ ለውጥ ነው ድርጅቶችን ወደ ታላቅነት የሚያደርሰው። ( ወድ ገጽ 4 ዞሯል)

## የታላቅ አምባገነን ተራ ሞት

መግለጫ ነሐሴ 15 2004

ሃያ አንድ ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲያጭበረብርና ሲያምታታ የኖረው መለስ ዜናዊ ሞትን ማጭበርበርና ማምታት አቅቶት መሸነፉ በቃል አባይ፣ ቃል አቀባዮቹ ግልጽ ሆኗል።

መለስ ይሙት እንጂ እሱ የዘረጋው የአፈና መዋቅርና የደነገጋቸው አፋኝ ህጎች ከመለስ ጋር አብረው አልተቀበሩም። በዘር ተሰባስበው ሃገርን የሚግጡና የሚረግጡ የጥቂት ግለሰቦች ቡድን ዛሬም በስልጣን ላይ ነው። መለስ የዘራው የዘር መርዝ መዘዙ እንደተዳፈነ ነው። ኅብረተሰባችን ወስጥ ያስፋፋው የሙስና ባህል እንደቆላ ቁስል ሃገር እየበላ ነው። ሃገሪቱና ዜጎቿ የገቡበት የውርደት ጉዞ እንደቀጠለ ነው። ድህነት፣ ስደት፣ የሙብት ረገጣ፣ አድሎ ከመለስ ዜናዊ ጋር አልተቀበሩም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ መለስ ዜናዊ በጫንቃው ላይ የከመረበትን እኩይና ክፉ የኑሮ ሸክም እንደተሸከመ ነው። በመሆኑም የመለስ ዜናዊን ሞት ከቁብ ቆጥሮ ይህን የግፍ ቀንበር ከላዩ ላይ ለማውረድ ከጀመረው የነጻነት ትግል የሚዘናጋበት ምክንያት የለውም።

በመለስ ዜናዊ ሞት የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያሳየው ግድየለሽነት ምንጩ መለስ ዜናዊ የማይሞት መስሎት በሕዝብ ላይ የፈጸመው በእብሪትና በጭካኔ የተሞላ ግፍ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ በመለስ ዜናዊ ሞት ዙሪያ የሃገር ውስጥና የውጭ ሃገራት ጥቅም ተካፋዮቹ የሚሰሩትን ትዕይንት በማየትና በመስማት የሚያጠፋው ግዜ አይኖርም። የሕዝብ ትኩረትና ጥድፊያ በመለስና መለስ ዜናዊ ጥሎት በሄደው አፋኝና ዘረኛ ሥርዓት መቃብር ላይ ሕዝብ ዝንተ ዓለም ሲመኘው የኖረውን በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት፤ ከነፃነትና ከሰብአዊ ክብር ጋር የተሳሰረ ብልጽግና እና የህግ የበላይነት የሰፈነበት ሃገር ለመገንባት ነው።

ታላቁ አምባገነን እንደማንኛውም ተራ ሟች የማይቀረውን የሞት ጽዋ ተጎንጭቷል። የሰበሰበው ሃብት፤ ያከማቸው ሠራዊትና መሣሪያ እና የአድናቂዎቹና የአጨብጫቢዎቹ ውዳሴ ከሞት አላስጣሉትም። ይልቁንም የፈጃቸው ንጹህ ነፍሳት እና ያሰቃያቸው ፍጥረታት ዋይታ አሁን ጎልቶ እየተሰማ ነው። በመለስ እግር ተተክተው አምባገነን ለመሆን ያሰፈሰፉት የወያኔ ሰዎች ከጌታቸው ፍጻሜ የሚማሩት ምንም ነገር እንደማይኖር እናውቃለን። ከቀደሙት አለመማር የአምባገነኖች ልዩ ባህርይ ነውና።

የመለስ ሞት እንደ መልካም አጋጣሚ መታየት የሚችለው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጀመረውን የነፃነት፣ የሙብትና የክብር ትግል አጠናክሮ መግፋት ከቻለ ነው። ግንቦት7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ለሕዝብም ሆነ ፣ለፖለቲካና ለሲቪክ ማኅበራት የሚያስተላልፈው መልእክት የሚከተለው ነው: -

*“ተነሱ እንተባበር! መለስ ዜናዊ የገነባውን ዘረኛና አምባገነን ሥርዓት ከመለስ ዜናዊ ጋር እንቅበረው!!!”*

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ተቃዋሚ ድርጅቶች ያለፈዉ የግፍ ስርአት ተመልሶ የማይመጣ ...

(ከገፅ 1 የዞረ)

በመጨረሻም ባለፉት አራት አመታት በሊቀመንበርነት የሚመሩት የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ኢትዮጵያ ውስጥ የስልጣን ክፍተት ቢፈጠር የተለያዩ ተቃዋሚ ድርጅቶችንና የኢትዮጵያን ህዝብ አስተባብሮ አመራር መስጠት የሚያስችል ድርጅታዊ ብቃት ማጎልበቱን በሙሉ ልብ ተናግረዋል።

የንቅናቄያችን ዋና ጸሃፊ የሆኑት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ባደረጉት አጭር ቃለ መጠይቅ የመለስ ዜናዊ ከህወሃት መድረክ መጥፋት ወያኔን ክፉኛ ሊያዳክመው እንደሚችል ገልጸው ሆኖም ይህ የተዳከመው ሃይል ከመለስ ዜናዊ በባሰ አፈናና ጭቆና ለመግዛት ከማሰብ እንደማይታቀብ ግልጽ ሊሆን እንደሚገባ አስታውቀው መፍትሄው ተቃዋሚዎች የሆን ሁሉ ከህዝባችን ጋር አንድ ሆነን ወያኔን ለማስገደድ ወይም ለማስወገድ የጀመርነውን ትግል ማፏፏም ነው ብለዋል።

## ኢትዮጵያ ጳጳስዋን እና መሪዋን በአንድ ሳምንት . . .

(ከገፅ 1 የዞረ)

ይህ በእንዲህ እንዳለ የመለስ ዜናዊን ሞት ተከትል ሊኖር የሚችለዉ የስልጣን ሽግግርና የኢትዮጳያ የወደፊት አቅጣጫ ምን ይሆናል የሚለዉ ጥያቄ የፈጠረዉ ስጋትና አለመረጋጋት አገሪቱን እያመሳት መሆኑን አዲስ አበባንና ዴሬደዋን ጨምሮ በየክልሉ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች ገለጹ።ኢትዮጵያ ዉስጥ ሰንደቅ አላማዎች በየቦታዉ ዝቅ ብለዉ እንዲዉለበለቡ በማድረግና በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የመለስ ዜናዊን ታላቅነት በማወጅ ህዝብን የማረጋጋት ስራ ለመስራት ቢሞከርም ከመለስ ዜናዊ ሞት ይልቅ የሀገሩ የወደፊት አቅጣጫ አለመታወቅ የጨነቀዉ የኢትዮጵያ ህዝብ በየክልሉ መረጋጋት አቅቶት በመዋተት ላይ መሆኑን ከኢትዮጵያ የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ።

የግንቦት ሰባት ድምፅ በቀጥታ ስልክ ደዉሎ ካናገራቸዉ የተለያዩ ሰዎች በተገኘዉ መረጃ መሠረት ኢትዮጵያ ዉስጥ በየቀበሌውና በየወረዳዉ ከፍተኛ የህዝብ መደናገጥና አለመረጋጋት ይታያል። አብዛኛዉ ተጠያቂ እንደተናገረዉ በብዙ የገጠር አካባቢዎች የቀበሌ ማህበራትና መንግስታዊ ድርጅቶች የሚሰጡት አግልግሎት ተቋርጧል። እንዲሁም የግልና የመንግስት ባንኮች ግራ በተጋቡና ገንዘባቸዉን ለማዉጣት በሚጣድፉ ሰዎች ተጨናንቀዋል ብለዋል። ባጠቃላይ የፌዳራልና የልዩ ጥበቃ ሀይሎች በከተማና በገጠር በየቦታዉ ተሰማርተዉ በከፍተኛ ጥበቃ ላይ እንደሚገኙና ይህም ሁኔታዉን ይበልጥ እንዳባባሰዉ በሰልክ አስተያየታቸዉን የሰጡን ሰዎች ሁሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ጭንቀትና ስጋት ከመጤፍ የማይቆጥረው የነበረከት ቡድን ግን የመለስ ዜናዊን ቦታ በጊዜያዊነት ለይስሙላ ምክትሉ ሃይለማሪያም ደሳለኝ መስጠቱን በፓርሊማ ተብዬው የካዴሬዎች ሸንጎ ለማስጸደቅ በዛሬው ዕለት አስቸኳይ ስብሰባ መቀመጡ ታውቋል።

በአፈጉባዔው አባዱላ ገመዳ የተጠራው ይህ አስቸኳይ ስብሰባ ሸንጎው በእረፍት ላይ እያለ መሆኑ ይታወቃል።

## ከጥሩ ወደ ታላቅ . . .

(ከገፅ 3 የዞረ)

መሻሻል በታየ መጠን አባላትም ይበረታታሉ። ቀጣዩ ዙር የሚጠይቀው ጉልበት ከበፊተኛው በጣም ያነሰ ይሆናል።

ሰዎች ከአሸናፊው ወገን መሆን ይፈልጋሉ። የሚታዩና ለሚጨበጡ ውጤቶች አስተዋጽዖ ማድረግ ይፈልጋሉ። ውጤት በሚያመጣ ነገር ውስጥ ተሳታፊ የመሆን ጉጉት አላቸው። ይህ የብዙ ቀና ሰዎች ፍላጎት ነው።

ሰዎች ጉራ ያልበዛበት፣ ሃቅን ያገናዘበ እቅድ ሲያዩ “ይኸ ይሠራል” ይላሉ። የሥራ አስፈፃሚው ቡድን ለእቅዱ በአንድነትና በጽናት ቆሞ ሲያዩ፤ አምስተኛ እርከን ላይ ያሉ መሪዎቻቸውን ሲመለከቱ ምፀታቸውን ትተው የምር ማሞካሸት ይጀምራሉ። መዘውሩ መሽከርከር ሲጀምር ብዙ ሰዎች መዘውሩን ለመግፋትና ፍጥነቱ እንዲጨምር የማድረግ ፍላጎት ያድርባቸዋል።

ወደ ታላቅነት ለመሸጋገር ባልታደሉ ድርጅቶች ውስጥ የሚስተዋለው ግን ከዚህ እጅግ በጣም የተለየ ነው። እዚያ ሁሌም የሚዘለል መሰናክል ነው ያለው። ቀስ እያለ ጀምሮ ሳያቋርጥ ከሚሽከረከር መዘውር ይልቅ የሚዘለሉ አጥሮች ያሉበት ነው።

ወደ ታላቅነት ለመሸጋገር ባልታደሉ ድርጅቶች ውስጥ “ታላቅ እመርታ” ተዓምራዊ መስፈንጠር” “የማያዳግም እርምጃ” የሚሉ ሃረጎች ይወደዳሉ። ፉከራና ቀረርቶ ቢበዛባቸውም ሲነሱ ጀምሮ ለውድቀት የተዘጋጁ ናቸው። እነዚህ ድርጅቶች መዘውር ቢሰጣቸው እንኳን በጀመሩት አቅጣጫ መግፋትን አይቀጥሉበትም። መዘውሩን ገፍተው መንቀሳቀስ ሲጀምር ደክመው ሊያቆሙ ይችላሉ፤ ወይም በአንድ አቅጣጫ ማዞር ከጀመሩ በኋላ ሃሳባቸውን ቀይረው በሌላ አቅጣጭ ደግሞ ይጀምራሉ። የሚዞረውን ሲያቆሙ፤ እንደገና ሲጀምሩ ባሉበት እንደቆሙ ይቀራሉ።

### ማጠቃለያ

አንድን ድርጅት ከጥሩነት ወደ ታላቅነት ለማሸጋገር ተገቢ ሰዎችን ብቻ ይዞ መነሳት ይኖርበታል። የተገቢው ሰዎች መኖር በተለይ የመዘውሩ የመጀመሪያ ዙር ለመግፋት ወሳኝ ነው። በአንድ ጊዜ ለሚገኝ ሳይሆን ቀስ ተብሎ ለሚደረስበት ውጤት ትዕግሥትን ጽናት ያላቸው ሰዎች መኖራቸው ወሳኝ ጉዳይ ነው።

የድርጅቱ አመራርም ሆነ አባላት ኃይላቸውን፣ ችሎታቸውን፣ ፍላጎታቸውን ሰብስበው በዋነኛ ሥራቸው ላይ አትኩረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ጃርት በእሾሆችዋ የመጠቀም ችሎታዋ የቀበሮን ብልጠት ለማሸነፍ ያስቻላት የመሆኑ ተምሳሌት ልብ ማለት ይገባል።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ሥነሥርዓት - ዲሲፐሊን - ከሌለ ሁሉም ነገር ዋጋ እንደሌለው መረዳት ይገባል። የአስተሳሰብ ዲሲፐሊን፣ የሥራ ዲሲፐሊን፣ የመዋቅር ዲሲፐሊን። ድርጅት ያለ ዲሲፐሊን ድርጅት አይደለም። ድርጅታዊ ዲሲፐሊን ወደ ባህል ደረጃ ካላደገ ደግሞ ፋይዳው እምብዛም ነው።

ይህ ሁሉ ከተደረገ ግን እንኳንስ ጥሩ ድርጅት መጥፎ ድርጅትንም ቢሆን ወደ ታላቅ ድርጅትነት ማሸጋገር ይቻላል። እርግጥ ነው አንድን ድርጅት በአንድ ወር ቀርቶ በአንድ ዓመትም ታላቅ ማድረግ ላይቻል ይችላል። መዘውሩ እየተሽከረከረ እስከሆነ ድረስ ግን ጊዜ ቢወስድም ይደረሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፐሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org